# CULTURAL HERITAGE PROTECTION HANDBOOK 2

# CARE AND HANDLING OF MANUSCRIPTS

## የጥንታዊ መጻሕፍት አጠባበቅና አያያዝ



UNESCO

Reproduction is authorized, providing that appropriate mention is made of the source, and a copy sent to the UNESCO, address below. This document should be cited as:
© UNESCO, 2006. Cultural Heritage Protection Handbook N° 2. Care and Handling of Manuscripts, UNESCO, Paris

**ይህን መጽሐፍ እንደገና ማሳተም የተፈቀደ ነው፣ ሆኖም ግን በትክክለኛው መንገድ ምንጭ መጠቀስና ኮፒ ለዩኔስኮ በሚከተለው አድራሻ መላክ ይኖርበታል**
**© የዩኔስኮ 2006 የባህላዊ ቅርሶች ጥበቃ መፅሐፍ ቁጥር 2 የጥንታዊ መጻሕፍት አጠባበቅና አያያዝ፣ ዩኔስኮ ፓሪስ**

Division of Cultural Objects and Intangible Heritage, Section of Museums and Cultural Objects
Text by : Antonio Mirabile
Drawings by : Beatrice Beccaro Migliorati

**የባህላዊ ጉዳዮችና የማይዳሰሱ ቅርሶች ክፍል፣ የሙዚየሞችና የባህላዊ ጉዳዮቸ ክፍል**
**ጽሁፍ ፡- አንቶኒዮ ሚራቢል**
**ሥዕል ፡- ቤአትሪስ ቤካሮ ሚግሊኦራቲ**

Amharic version
Translation by : Mamitu Yilma, National Museum of Ethiopia
Tiguist Asfaw, UNESCO Addis Ababa Office

**የአማርኛ ትርጉም**
**ትርጉም፡- ማሚቱ ይልማ፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሙዝየም**
**ትዕግስት አስፋው፣ ዩኔስኮ አዲስ አበባ ጽ/ቤት**

Printed in 2007 by the :
United Nations Educational, Scientific and Cultural Organization

**እ.ኤ.አ 2007 ታተመ**
**የተባበሩት መንግስታት የትምህርት የሳይንስና የባህል ድርጅት**

UNESCO Addis Ababa Office
ECA New Building 1st floor
P.O.Box 1177 Addis Ababa, Ethiopia
© UNESCO 2006 (CLT/CH/MUS –06/18)

**ዩኔስኮ አዲስ አበባ ጽ/ቤት**
**ኢሲኤ አዲሱ ሕንፃ 1ኛ ፎቅ**
**የ.መ.ሣ.ቁ. 1177 አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ**
© **ዩኔስኮ 2006 እ.ኤ.አ** (CLT/CH/MUS –06/18)

# INTRODUCTION

This booklet is intended for all who collect and are fond of manuscripts, as well as those in charge of public or private collections of manuscripts and rare books.

The principles given here concerning the preservation of manuscripts can also be applied to printed books and bound documents.

Certain measures concern institutions with equipment and personnel not within the means of private individuals. However, these recommendations constitute a sort of ideal which one should endeavour to reach as far as possible.

ይህ መጽሐፍ ጥንታዊ ጽሑፎችን/መጻሕፍትን ለሚሰበሰቡና የተለየ ፍቅር ላላቸው ፤እንዲሁም ሕዝባዊም ሆነ የግል የጥንታዊ ጽሑፍ ስብስቦችንና ለየት ያሉ መጻሕፍትን ለሚያሰባስቡ ታስቦ የተዘጋጀ ነው::

የጥንታዊ መጻሕፍት ጥበቃን በተመለከተ እዚህ የተሠጡ መመሪያ ዎች፣ ለታተሙ መጻሕፍትም ሆነ ለተጠረዙ ሰነዶች ያገለግላል::

አንዳንዶቹ እርምጃዎች የሚመለከቱት የተሟላ ዕቃዎችና ባለሙያዎች ለተሟሉላቸው ተቋማት እንጂ አማራጭ ለሌላቸው የግል ተቋማትና ግለሰቦች አይሆንም:: ሆኖም ግን እዚህ የተቀመጡት ሀሳቦች አንድ ሰው መዳረስ የሚፈልገው ድረስ ሊያስኬዱት ይችላሉ::

# OCCIDENTAL MANUSCRIT




| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | Spine / Back | 7 | Squares | 1 | የጥራዝ ጠርዝ | 7 | ግሌት |
| 2 | | 8 | Edge | 2 | ጥራዝ | 8 | ግሌት |
| 3 | Cord | 9 | Head | 3 | ኩተት | 9 | ርዕስ |
| 4 | Tail | 10 | Headband | 4 | የገበታ እግር | 10 | ቆታን |
| 5 | Board | 11 | Shoulder | 5 | ገበታ | 11 | የቆታን ጉንጉን |
| 6 | Fore Edge | 12 | Guard-leaf | 6 | አፈ መጽሐፍ | 12 | ግላፍ |

# ARABIC MANUSCRIT




| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | Flap | 6 | Headband/Endband | 1 | ልባስ | 6 | ርዕስ |
| 2 | Upper Board | 7 | Head | 2 | ሐረግ | 7 | ርዕስ |
| 3 | Decoration/Tooling | 8 | Lower board | 3 | ድጉስ | 8 | የገበታው ራስጌ ጠርዝ |
| 4 | Tail | 9 | Fore edge | 4 | የጥራዝ ጠርዝ | 9 | አፌ መጽሕፍ |
| 5 | Spine | 10 | Guard-leaf | 5 | ጥራዝ | 10 | የገበታው አካልና የወረቀተቶች መጀመሪያ የሚጋጥሙበት ከንፈር |

**ለአማርኛው ትርጉም ዝርዝር መረጃ ገፅ 44 ተመልከት**

# LIBRARY AND RESERVE COLLECTION ROOMS

# የቤተ መጻሕፍትና የመጠባባቂ ክምችት ክፍሎች




Stabilize air-conditioning parameters in the library and reserve collection rooms (relative humidity between 50 and 60% and temperature between 16 and 20°C).

በቤተ መፃህፍቱና በመጠባበቂያ ክምችት ክፍሎች ያለውን የአየር መቆጣጠሪያ አስተካክል (የእርጥበት መጠኑ በ50 እና በ60% እና የሙቀት መጠን በ16 እና 20 ሴንቲ ግሬድ መሀከል መሆን ይኖርበታል)::




Check air-conditioning parameters at regular intervals.

የአየር መቆጣጠሪያውን በተወሰነ ሰዓት ተቆጣጠር::



Check that doors and windows are tightly closed.
*ment.*

በሮችና መስኮቶች በጥብቅ መዘጋታቸ ውን አረጋግጥ።



Use blinds, screens and shutters to protect documents against sunlight.

መረጃዎችን ከፀሐይ ብርሃን ለመከላከል የተለያዩ መጋረጃዎችንና መከላከያዎችን ተጠቀም።



Fit all openings with a grid. Use a grid with sufficiently fine mesh to keep insects out while not restricting airflow.

ሁሉንም ክፍል ቦታዎች በሽቦ ወንፊት ሸፍን፡፡ ሽቦው ነፍሳት እንዳይገቡበት ጥቅጥቅ ያለ መሆን ሲኖርበት፣ ግን አየር ማስገባት መቻል ይኖርበታል፡፡



Pipes and ducts should not pass through library and reserve rooms. Provide an emergency evacuation plan to be applied in the event of flooding.

ቧንቧዎችና የኤሌክትሪክ ማስተላለፊያዎች በቤተ መጻሕፍትና በክምችት ክፍሎች ውስጥ ማለፍ የለባቸውም፡፡ የጐርፍ አደጋ በሚያጋ ጥምበት ጊዜ የአስቸኳይ የአደጋ ጊዜ መውጫ ፕላኖችን አቅርብ/ተግባራዊ እንዲሆኑ አድርግ፡፡




Insulate"*" electrical systems, avoiding loose wires.

የተለያዩ የኤሌክትሪክ ሽቦዎችን በመተው፤ የኤሌክትሪክ ሲስተም እንዲለይ አድርግ::



Provide fire detection and fighting equipment; define measures to be taken at outbreak of fire.

የእሳት መቆጣጠሪያ ማጥፊያ መሳሪያዎችን አሟላ፣ የእሳት አደጋ ባጋጠመ ጊዜ መወሰድ ስላለባቸው እርምጃዎች በግልፅ አስፍር/አስ ቀምጥ::

## LIBRARY AND RESERVE COLLECTION ROOMS
## የቤተ መጻሕፍትና የመጠባበቂያ ክምችት ክፍሎች



Clean library and reserve rooms at regular intervals. Remove dust with vacuum cleaners fitted with total filtration, then wipe with damp floorcloth (once a week).

በተወሰኑ ጊዜያት የቤተ መጻሕፍቱን የክምችት ክፍሎች አፅዳ፣ አቧራውን ቫኪዩም ክሊነር በመጠቀም አስወግድ፤ ወለሉን እርጥበት ባለው መወልወያ በሳምንት አንድ ጊዜ አፅዳ፡፡



Inspect reserve rooms and manuscripts at regular intervals. Train personnel to inspect reserve rooms and manuscripts regularly for mould, dust, insects and rodents.

የመፅሐፍ ክምችቶች ያሉባቸውን ክፍሎችና ጥንታዊ መጽሐፍትን በተወሰኑ ጊዜያት መቆጣጠር፤ በክምችት ውስጥ ያሉ መፃህፍት በሻጋታ፣ በአቧራ፣ በነፍሳትና በአይጦች እንዳይበላሹ ክትትል የሚ ያደርግ ባለሙያ ማሰልጠን፡፡



Store waste far from library.

ቆሻሻዎችን ከቤተ መጻሕፍቱ አርቀህ አስቀምጥ።



Store manuscripts in the dark (or turn off the lights when you leave the library).

ጥንታዊ መጻሕፍትን በጭለማ ክፍል እንዲ ቀመጡ አድርግ፤ (ወይም መፅሐፍቱ ያሉ በትን ክፍል መብራቶች ስትወጣ አጥፋ)።




New acquisitions"1" should be examined by a specialist before being added to the collection. Isolate"2" affected books to reduce risk of general contamination.

አዲስ የገቡ መጻሕፍት ከሌላው ስብስብ ጋር ከመካተታቸው በፊት በባለሙያ እንዲታዩ ማድረግ፣ የተበከሉ /የተበላሹ/ መጻሕፍት ለሌሎች ብክለትን የማስተ ላለፍ አደጋ ለመቀነስ ለይቶ ማስቀመጥ::

# FURNITURE
# ቁሳቁስ




Stock the library with painted"2,3" shelves (if possible in metal)"1", free of cutting edges and bulges.

መጻሕፍቱን በተቀቡና ጫፋቸው ከመ ቅደድና ከማበጥ ነፃ በሆኑ መደር ደሪያዎች /ቢቻል በብረት መደርደሪያ/ እንዲቀመጡ አድርግ::



Spacing of shelves should be sufficient to allow proper circulation of air.

የመጻሕፍት መደርደሪያዎች አቀማ መጥ፤ የአየር በተገቢው ሁኔታ ለመ ተላለፍ በቂ መሆን ይኖርበታል።



The lower shelf should be at least 15 cm above floor level in order to protect books against damp and rodents.

መጻሕፍትን ከእርጥበትና ከአይጦች ለመ ከላከል የታችኛው መደርደሪያ ከወለሉ 15 ሳ.ሜ ከፍ ያለ መሆን ይኖርበታል።



Keep a gap of at least 5 cm between shelves and wall.

በግድግዳውና በመደርደሪያዎቹ መሀከል ቢያንስ 5 ሳ.ሜ ክፍተት /ልዩነት/ ጠብቅ::



Shelves should be closed by a panel at the top to protect documents against dust.

ሰነዶቹን ከአቧራ ለመከላከል የመደርደሪያዎች አናቶች በፓነል መዘጋት ይኖርባቸዋል::



Avoid shelves that are too high, as manuscripts should be within easy reach.

ጥንታዊ መጻሕፍት የሚቀመጡበት ሥፍራ በቀላሉ የሚደረስበት መሆን ስለሚኖርበት፣ በጣም እረዣዥም /ከፍተኛ / መደርደሪያዎች አስወግድ።

# BOOK STORAGE
# የመጽሐፍ ክምችት



Never store books or manuscripts on floor.

መጻሕፍትና ጥንታዊ መጻሕፍትን በጭራሽ ወለል ላይ እንዲቀመጡ / እንዲከማቹ /አታድርግ።

**BOOK STORAGE**
**የመጽሐፍ ክምችት**



Do not store books on their fore edge or spine. As this may place undue pressure on spine and binding.

**መጻሕፍትን በጫፋቸው ወይም በጀርባቸው አታስቀምጥ ፤ ምክንያቱም ይሄ አቀማመጥ የጥራዝ ጠርዙና ጥራዙ ላይ አላስፈላጊ ጫናን ሊፈጥር ስለሚችል ነው።**



Do not let books protrude beyond shelf edges. Books might be damaged by passing trolleys or persons.

**መጻሕፍት ከመደርደሪያው ጫፍ አልፈው /ተርፈው/ እንዲቀመጡ አታድርግ፣ ምክንያቱም በሚተላለፍ ሰው ወይም የመፃህፍት ማመላለሻ ጋሪዎች አደጋ ሊደርስባቸው ስለሚችል።**



Store manuscripts, rare and / or deteriorated books in suitable boxes, laying them flat.

ልዩ የሆኑ ጥንታዊ ጥንታዊ መጻሕፍት ወይም የተጐዱ መጻሕፍትን አመቺ በሆነ የማስቀመጫ ሳጥን ውስጥ ዝርግ በሆነ አቀማመጥ አስቀምጥ።



Store books with metal parts in tailor-made boxes specially designed for these volumes. If stored on shelves, the metal parts are likely to damage books stored on either side.

በብረት የተለበጡ መጻሕፍትን ለዚሁ አላማ በተዘጋጁ ሳጥኖች ውስጥ አኑር፣ በመደርደሪያ ላይ ቢቀመጡ አጠገባቸው የሚገኙትን ሌሎች መጻሕፍት ሊጐዱ ይችላሉ።



Lay large volumes flat; stack no more than three or four books of the same format.

ትልልቅ ጥራዞችን ዝርግ በሆነ ሁኔታ እንዲቀመጡ አድርግ፤ ተመሳሳይ የሆኑ ከሶስትና ከአራት ጥራዞች ያልበለጡ መጻሕፍትን በአንድ ላይ አስቀምጥ።



Only small books in good condition may be stood upright with book ends. Book ends should be smooth and have large angles.

በጥሩ ሁኔታ ላይ የሚገኙ ትንንሽ መጻሕፍት በቁመታቸው እንዲቀመጡ ማድረግ፣ ሆኖም ግን የመጻሕፍቱ ጠርዝ ለስላሳና ተለቅ ያለ አንግል ያለው መሆን ይኖርበታል።



Do not stand small format books next to large format. This might leave large format books without sufficient support.

ትንንሽ መጻሕፍትን ትላልቅ መጻሕፍት አጠገብ አታስቀምጥ፣ ይሄ አቀማመጥ ትላልቅ መጻሕፍት ካለ በቂ ድጋፍ እንዲቀመጡ ያደርጋቸዋል።



Do not tighten or space books excessively on shelves.

መጻሕፍትን በመደርደሪያው ላይ ተጨ ናንቀው ወይም ክፍተት ኖሯቸው እንዲ ቀመጡ አታድርግ።



Leaning books are inclined to bend.

ያጋደሉ መጻሕፍት ሊጐብጡ ይችላሉ::




Keep of at least 5 cm space between books and the rear panel.

ከመጽሐፍ መደርደሪያው ፓነል ጀርባና በመጻሕፍቱ መካከል የ 5 ሳ.ሜ ክፍተት እንዲኖር አድርግ::



Store leather bindings separately from paper/cardboard and cloth bindings. Tanned and acid leather might soil paper and fabric bindings.

የቆዳ ጥራዞችን፣ ከወረቀት፣ ከእንጨትና ጨርቅ ጥራዞች ለይተህ አስቀምጥ፣ በፀሐይ የተጐዳና አሲድ ይዘት ያለው ቆዳ የወረቀትና የጨርቅ ጥራዞችን ሊያበላሽ ይችላል::

# HANDLING
# አያያዝ



Wash and dry hands prior to handling. Cotton gloves are highly recommended.

መጻሕፍት ከመያዝ በፊት እጅህን ታጥበህ አድርቅ፣ ከጥጥ የተሠሩ ጓንትን መጠቀም በጣም ተፈላጊነት አለው /ይመረጣል::



Provide space where to lay down the books moved.

ለተነሱ መጻሕፍት ማስቀመጫ ሥፍራ ማዘጋጀት።



Do not pull the books out by the head cap. This could loosen the spine.

መጻሕፍትን ሲያወጡ በርዕሱ አለመሳብ፤ ይህ የጥራዝ ጥራዙን ሊያላቅቀው ይችላል።



Grasp the book at centre of spine while moving aside the volumes next to it and slightly lifting it.

የመጽሐፉን ጥራዝ ጠርዝ መሐከል ላይ በመያዝ ከአጠገቡ ያለውን መጽሐፍ እልፍ በማድረግ ትንሽ ከፍ አድርገህ አንሳው።



If there is sufficient space above, slide the book towards you on its fore edge.

ከላይ በቂ ቦታ ካለ አፊ መጽሐፉን በመያዝ ወደ ራስህ በማጋደል አንሳው።



Never force a book into its shelf position.

መጻሕፍትን በጭራሽ በኃይል መደርደሪያው ውስጥ ገፍተህ ለመክተት አትሞክር።



Open the manuscript carefully. Lay the manuscript down on a table…

ሰነዱን በጥንቃቄ ክፈት ፤ በጠረጴዛ ላይ አስቀምጠው...



…first open the centre pages…

… መጀመሪያ የመጽሐፉን መሐከል ክፈት …



…then go back to the beginning.

… ቀጥሎ ወደ መጀመሪያው ገፅ ተመቀስ::

# DUST REMOVAL
# የአቧራ አነሳስ




Perform dust removal"1" in a room at some distance from library or reserve"2".

የአዋራ ማስወገድ ተግባርን ከቤተመጻሕፍቱና ከክምችት ክፍሉ ራቅ ብሎ በሚገኝ ክፍል አከናውን፡፡




Use a vacuum cleaner fitted with a total filtration system, a power adjustor"*" and a soft brush.

የማጣሪያ ሲስተም ፤የኃይል ማስተካከያና ለስላሳ ብሩሽ ባሉት ቫኪዩም ክሊነር ተጠ ቀም፡፡



Do not use a vacuum cleaner on manuscripts in poor condition or having fragile parts.

በተጐዳ አያያዝ ላይ ያሉና የተጐዱ ክፍሎች ባላቸው ጥንታዊ ጽሑፎች ላይ ቫኪዩም ክሊነር አትጠቀም።



Begin dust removal on outside of volume without letting it lodge in corners.

የአዋራ ማስወገዱን ተግባር ከመጻሕፍቱ /ከጥራዙ/ በስተውጭ በኩል ጠርዙን ሳይነካ ጀምር።

## DUST REMOVAL
## የአቧራ አነሳስ



Remove dust from flyleaves and first and last section of the book block using a large, soft brush. Hold manuscript at an angle and make dust slide down to lower edge.

ትልቅ ለስላሳ ብሩሽ በመጠቀም አቧራውን ከመጽሐፍ ቅጠሎች /ገጾች/ የመጀመሪያና የመጨረሻ ክፍሉ ላይ አንሳ፤ ጥንታዊ መ ጻሕፍትን በእጅህ በአንግል በመያዝ አቧራው ከላይ ወደታችኛው ግሌት እንዲወርድ አድርግ።



Before returning manuscript to shelf, clean the latter with a vacuum cleaner and a damp cloth.

ሰነዶቹ ወደ መደርደሪያው ላይ ከመመለስህ በፊት፤ መደርደሪያውን በቫኪዩም ክሊነርና እርጥበት ባለው ጨርቅ ወልውል/አፅዳ።

# TRANSPORT
# ማጓጓዝ



Transport manuscripts lying horizontally in a box.

ጥንታዊ መጻሕፍትን በሳጥን ውስጥ በአግድም እንዲቀመጡ አድርገህ አጓጉዝ::



Carry only a limited number of manuscripts at a time (three or four).

በአንድ ጊዜ የተወሰነ ቁጥር ያላቸውን ጥንታዊ መጻሕፍትን ተሸከም /ሶስት ወይም አራት/::



Heavy manuscripts should be moved by trolley.

ክብደት ያላቸው መጻሕፍትን በጋሪ /ትሮሊ/ ማጓጓዝ።



Use a trolley fitted with large rubber wheels. Such wheels keep the manuscripts in a stable position and absorb vibrations.

ትልቅ የላስቲክ ጐማዎች ያሉት ጋሪ ተጠቀም፤ እንደዚህ ዓይነት ጐማዎች ጥንታዊ መጻሕፍትን በተረጋጋ ሁኔታ እንዲቀመጡ ሲያደርግ፣ መርገብገብንም መቆጣጠር ያስችላል።



Make sure that manuscripts do not protrude over side of trolley.

ጥንታዊ መጻሕፍቱ ከጋሪው አለመትረፋቸውን አረጋ ግጥ።



Never place a large volume on a smaller one. Non-observance of this recommendation may cause the large book to fall on the floor during transport.

በጭራሽ ትልቅ መጻሐፍ በትንሹ ላይ አታስ ቀምጥ፤ ይሄን አለማድረግ በሚጓጓዝ ጊዜ ትልልቁ መሐፍት እንዲወድቅ ያደርጋል።

## TRANSPORT
## ማጓጓዣ



For any extramural transport (into another building), use hermetically sealing boxes.

ከአንድ ሕንፃ ወደ ሌላ ሕንፃ በምታዘዋው ርበት ጊዜ የሚታሸጉ/የሚዘጉ ሳጥኖችን ተጠቀም::

# CONSULTATION
# ምክር




Do not leave manuscripts in poor condition available for consultation" * ".

የተጐዱ ጥንታዊ መጻሕፍትን ለእይታ/ ለምርምር እንዲ ውሉ አታድርግ::



Display the basic rules for handling. Provide for surveillance of consultation room.

መሠረታዊ የሆኑ የአያያዝ ስርአቶችን አሳይ፤ መረጃዎች የሚታዩበት ክፍል የቅኝት/የምልከታ መሳሪያ ይኑር።



Wash and dry hands before handling manuscripts.

መጻሕፍትን ከመያዝህ በፊት እጅህን ታጥበህ አድርቅ።



Do not drink, eat or smoke in library or reading room.

ቤተመጻሕፍት ወይም ማንበቢያ ክፍል ውስጥ መጠጣት/መብላትና ማጨስ የለብህም።



To consult a manuscript, lay it on a clean table free of any object, or use a book-rest suited to size of volume.

ጥንታዊ መጻሕፍትን በምታይበት ጊዜ ምንም ነገር ያልያዘ ነፃ የሆነ ንፁህ ጠረጴዛ ላይ ወይም በመጽሐፍ ልክ በተሠራ ማስቀመጫ ላይ አድርገህ ተጠቀም፣



Open the manuscript gradually. Lay it on a table…

መጽሐፍን ቀስ ብለህ ግለጥ፣ ጠረጴዛ ላይ አስቀምጠው ...



… first open the centre pages…

... መጀመሪያ የመሐሉን ገፆች ግለጥ ...



…then go back to the beginning.

**… ቀጥሎ ወደ መጀመሪያው መመለስ።**



Do not place manuscripts facing a window and do not expose to direct sunlight.

**ጥንታዊ መጻሕፍትን በመስኮቱ ፊትለፊት በኩል እንዲቀመጡና ለቀጥታ የፀሐይ ጨረር እንዲጋለጡ አታድርግ።**



Do not stack open manuscripts.

**የተገለጡ ጥንታዊ መጻሕፍትን አታደራርብ /ደራርበህ አታስቀምጥ።**



Do not tear or cut pages.

**ገጾችን አትቁረጥ፣ አትቅደድ።**



Do not mark manuscripts in any way whatever (paper clip, needle, post-it®, ink, ball-point pen, correction fluid, marker) or turn down the corner of a page, etc...

ጥንታዊ መጻሕፍት ላይ በምንም አይነት መልኩ ምልክት አታድርግባቸው /የወረቀት ማስ ያዥ፣ መርፌ፣ መልዕክት መያዣ ወረ ቀት፣ ብዕር፣ እስክሪፕቶ፣ የማረሚያ ፍሉድ፣ ማርከር /ወይም የመፅሐፉን ገጽ ጫፍ ማጠፍ ወዘተ...



To write down notes, only pencils are authorized.

ማስታወሻ ለመፃፍ የተፈቀደው በእርሳስ ብቻ ነው::



Do not lean on manuscripts while reading them or taking notes.

በምታነብበት ወይም ማስታወሻ በምት ይዝበት ወቅት ጥንታዊ መጻሕፍት ላይ አትደገፍ፡፡



Do not touch illuminations/illustrations, or manuscript and printed areas.

ምሥል ያለባቸውን ወይም የሕትመቱን ክፍሎች በእጅ አትንካ፡፡



Do not photocopy manuscripts or take pictures without the consent of the owner or person responsible.

ከባለቤቱ ወይም ከኃላፊው ስምምነት ሳታገኝ ጥንታዊ መጻሕፍትን ኮፒ አታድርግ ወይም ፎቶግራፍ አታንሳ።



Close the manuscript after consultation.

ከተጠቀምክ በኃላ መጽሐፉን ክደን/ዝጋ።

# DISPLAY
# ለዕይታ ማቅረብ




Check state of preservation of manuscripts before displaying them.

ጥንታዊ መጻሕፍትን ለእይታ ከመቅረባቸው በፊት ያሉበትን የአያያዝ ሁኔታ አረጋግጥ::



If they are in good condition, you may expose them for a maximum of one month each year.

በጥሩ ሁኔታ ላይ የሚገኙ ከሆኑ በአመት ቢበዛ ለአንድ ወር ለእይታ አቅርብ::

## DISPLAY
## ለዕይታ ማቅረብ



Set the display room air conditioning parameters (relative humidity between 50 and 60% and temperature between 16 and 20°C).

የትርኢት ክፍሉ የአየር መቆጣጠሪያ አስ ተካክል (መካከለኛ እርጥበት በ50 እና 60% መሀከል፣ የሙቀት መጠን በ16 እና 20 ሴንቲ ግሬድ መካከል)::



Display manuscripts in safe showcases.

ጥንታዊ መጻሕፍቱን አስተማማኝ በሆነ የማሳያ ሳጥን ውስጥ በማስቀመጥ ለእይታ አቅርብ፣




Fit showcase panes"3" with anticaloric"2" and UV"1" filters.

የማሳያ ሳጥኖቹ የጨረር መከላከያ እንዲገጠምላቸው አድርግ፡፡



Place light source outside showcase.

መብራቶቹን ከማሳያ ሳጥኖቹ ውጭ አድርግ፡፡

## DISPLAY
## ለዕይታ ማቅረብ



The intensity of the light shall be limited to 50 Lux.

የብርሃን መጠን በ 50 ላክስ መወሰን ይኖርበታል::



Display manuscripts on book-rests made of or lined with neutral cardboard.

ጥንታዊ መጻሕፍቱን ከእንጨት/ ከካርቶን በተሰራ የመፀሐፍ ማስቀመጫ ላይ ሆኖ ለእይታ ማቅረብ::



The manuscript should be held open by polyester ribbons adapted to the profile of the manuscript.

ጥንታዊ መጻሕፍትን ከመፃህፍቱ ጋር በሚሄድ የፖሊስተር ሪቫን እንዲያዙ ማድረግ::




The opening angle shall not exceed 120° and the tilting angle, with respect to the horizontal plane, shall not exceed 20°.

የጥንታዊ መጻሕፍቱ የተከፈተው አንግል $120^0$ መብለጥ የለበትም፣ የሚያጋድልበት አንግል በአግድም ከ $120^0$ መብለጥ የለበትም::

**ክፍል፡ 1**

1. የጥራዝ ጠርዝ /ከላይ ወደታች ቀጥ ብሎ የወረደና የታጠፈ የገበታውና የወረቀቱ መገናኛ /
2. ጥራዝ ( በመጽሐፍ ጀርባ የሚታይ ክፍት ቦታ /አጠቃላይ ጥራዝ ይባላል)
3. ኩተት ( የመጽሐፍ የውስጥ ወረቀቶች በክር የተያያዙበት ፣)
4. የገበታ እግር (የመጽሐፍ ገበታ ጣናና የጥራዙ መገናኛ፣
5. ገበታ (የጣውላ ቁራጭ፣ እንጨት ወይም ካርቱን)
6. አፈ መጽሐፍ (የመፅሐፍ፣ ወረቀት ወይም ብራና የሚከፈትበትበት ጠርዝ )
7. ግሌት (የገበታ ዙሪያ ጠርዝ፣ ከፊት ለፊት)
8. ግሌት(የወረቀቶች ፣ብራናዎች የላይኛው ጠርዝ)
9. ርዕስ (በላይ በኩል የሚገኘው የገበታውና የጥራዙ አናት )
10. ቶታን (የጥራዙና የወረቀቶቹ ስፌት)
11. የቶታን ጉንጉን (ለቶታን የተዘጋጀው ቆዳ፣ ወይም ጨቆ ወዘተርፈየተጋደመለት
12. ግላፍ (የገበታውና የጽሑፍ መጋጠሚያ ወይም የመጽሐፍ ከንፈር)

**ክፍል ፣2**

1. ልባስ (የመጽሐፋ ከንፈር የሚሸፈንበት)
2. ሐረግ (የገበታ ጌጥ)
3. ድጉስ (በገበታው ላይ የሚታይ ሐረግና መሰል ጌጥ)
4. የጥራዝ ጠርዝ (የገበታ ጫፍና ወረቀቱ / ከብራናው የሚገናኙበት ጫፍ)
5. ጥራዝ (የጀርባው ክፍል) የሚጠራበት
6. ርዕስ (የጥራዝ መገናኛ ወይም የግራ ጠርዝ ራስ)
7. ርዕስ (የመጽሐፍ ራስጌ ክፍል)
8. የገበታው ራስጌ ጠርዝ
9. አፈ መጽሐፍ (የመጽሐፋ ወረቀቶች የሚከፈቱበት)
   የገበታው አካልና የወረቀቶች መጀመሪያ የሚጋጠሙበት ከንፈር